ክቡራን ቤተሰቦች

በሚመጣው የበጋ የእረፍት ግዜ መድሀኒቶችን ማስቀመጥ አንችልም። ልጅዎ በትምህርት ቤት የተቀመጠ መድሀኒት ካለው/ካላት እባክዎ አስታውሰው እስከ ጁን 26 ድረስ ይውሰዱ።

የ2019-2020 ትምህርት ወቅት በሚጀምርበት ግዜ ልጆችዎ ጥሩ እና ጤነኛ በሆነ መንገድ ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ከእርስዎ የምንፈልጋቸው የተወሰኑ ነገሮች አሉ። እነዚህን እስከ ኦገስት 20 እንዲያሟሉ እንጠይቃለን። የምንፈልጋቸው የሚከተሉትን ነው

- *የመድህኒት ቤቱ ስም ፅሁፍ ያለበት መድሀኒት*
- *መድሀኒቱን እንድንሰጥ ፈቃድ የሚሰጥ በወላጅ እና መድሀኒቱን ባዘዘው ዶክተር የተፈረመ ወረቀት*

*ማንኛውም ወደ ትምህርት ቤት የሚመጣ መድሀኒት በዶክተር የታዘዘም ቢሆን ከሱቅ የተገዛ፤ የተፈረመበት የሜዲካል ፎርም በትምህርት ቤቱ ፋይል ውስጥ መመዝገብ አለበት። እነዚህ ፎርሞች በኢሜል ወይም በፖስታ ይላካሉ።*

*ትምህርት የሚጀመርበት ግዜ ገና እንደሆነ ይገባናል፤ ግን እነዚህን የሚያስፈልጉ ነገሮች ለእኛ ለመስጠት በቂ ግዜ እንዲኖርዎት ብለን ነው። ጥያቄ ወይም ሀሳብ ካለዎት እባክዎ የልጅዎ ትምህርት ቤት ዋና መስሪያ ቤት እስከ ጁን 26 ይድውሉ።*

*ከምስጋና ጋር*

*የኤድመንድስ የትምህርት ዲስትሪክት የጤና አገልግሎት*